دار زايد للثقافة الإسلامية
Zayed House For Islamic Culture

# ዛይድ የሰብአዊ ድርጊቶች ቀን



يوم زايد للعمل الإنساني
حب ووفاء .. لزايد العطاء

## ዛይድ የሰብአዊ ድርጊቶች ቀን

በወርሃ ረመዷን 19ኛው ቀን በተባበሩት ዓረብ ኢምሬት የ"ዛይድ ሰብአዊ ድርጊቶችን ቀን" ይከበራል፡፡ ይህ ቀን የታላቁን መሪ፦ የሸይኽ ዛይድ ቢን ሱልጣን አል ናህያን ህልፈተ ህይወት ቀን ጋር ይገጣጠማል፡፡ (አኳህ ይማራቸው በጀነት ውስጥም ያኑራቸው፡፡) ይህን ቀን በማስመልከትም በአገሪቱ ውስጥና በአለም አቀፍ ደረጃም የተለያዩ ሰብአዊ የበጎ አድራጎት ፕሮጀክቶች መንግስታዊና ማህበራዊ በሆኑ ድርጅቶች ውስጥ በግልጽ ይፈጸማሉ፡፡ በዚህም የሸይኽ ዛይድን ተበጎ አድራጎት ውርስ በማሳተፍ የርሳቸውን መታሰቢያነት በልቦች ውስጥ ዝንተ ዓለም እንዲዘከሩ ያደርጋል፡፡

## ዛይድ የሰብአዊ ድርጊቶች ቀን ዓላማዎችና መርሆዎች፦

የ"ዛይድ ሰብአዊ ድርጊቶችን ቀን" የርሳቸውን ስብእና ለማስረጽ፣ ሰብአዊ መርሆዎቻቸውን በማህበረሰቡ ውስጥ ለማሰራጨት በየ ዓመቱ በረመዷን ወር ውስጥ ይመጣል፡፡ ይህን ስብእና ለማሳካትም በገሃድ የሚታዩ የሆኑ ሰብአዊ መርሆዎችንና ዓላማዎችን መንደርደሪያ ለማድረግና የቅርቡም የሩቁም እንዲጠቀምበት በማሰብ ተወስኗል፡፡

## እነዚህ መሠረታዊ ዓላማዎችም እንደሚከተሉት ይዘረዘራሉ፦

1. የተባበሩት ዓረብ ኢምሬት አገር መስራች የሆኑትን የሸይኽ ዛይድን ታሪካዊ መታሰቢያነት ማስረጽ.
2. ሰብአዊ ድርጊቶችን በማህበረሰቡ ውስጥ ማጠናከርና ማህበረሰቡን ለማልማት አስፈላጊነቱን ማጽደቅ.
3. በዓለም ውስጥ የሚገኙ ማህበረሰቦችን ስቃዮች መከራዎችና ችግሮች መታደግ.
4. የተሟላ ጥራት ያላቸውን ሰብአዊ ሥራዎችንና ፕሮጀክቶችን በአገሪቱ ውስጥ፣ በቀጠናዎችና በዓለም አቀፍ ደረጃም በመሪነት ማስጀመር.
5. የተባበሩት ዓረብ ኢምሬት በሰብአዊ በጎ አድራጎቶች ያላትን ዓለም አቀፋዊ ድርሻ ማበርታትና ማጎልበት.

ከላይ በተገለጸው መሠረት የ"ዛይድ ሰብአዊ ድርጊቶችን ቀን" የበጎ አድራጎት የፈጠራና የብዝሃነት እንዲሁም ማህበረሰቡ የበጎ አድራጎቶችን ሥራ በጽናት እንዲቀጥል የሚያበረታታ ቀን እንደሆነ ይቆጠራል፡፡ ይህም የተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ማህበራዊ ድርጅቶች በሚያዘጋጇቸው የበጎ አድራጎቶች ሥራ ፕሮግራሞች አማካይነት ይፈጸማል፡፡ ሰዎችን የማገልገልና ሰብአዊ በጎ አድራጎቶችን ባህል በመላው ዓለም ለማሰራጨትም ጭምር ነው፡፡

## የሸይኽ ዛይድ የሰብአዊ ድርጊቶች አርአያ፦

ሸይኽ ዛይድ (አኳህ ነፍሳቸውን በጀነት ያኑረውና) በመላው ህይወታቸው በአገር ውስጥ በክልል አገሮችና በዓለም አቀፍ ደረጃም የበጎ አድራጎቶች ግንባር ቀደም ርእስ ነበሩ፡፡ በዓለም ላይ የሚገኙ የተለያዩ ማህበረሰቦች የርሳቸውን ለጋስና ቸር እጆች ሁሌም ያስታውሳሉ፡፡ ይህንንም በአገራቸው ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ከተሞችን መንገዶችን ጎዳናዎችን ሆስፒታሎችን ዩልደዮችንና ትምህርት ቤቶችን በርሳቸው ስም በመሰየም ያረጋግጣሉ፡፡ ታሪክም ይህን የርሳቸውን ጥበባዊ አባባል፦ "እኛ አኳህ የሰጠንን ጸጋ ለሌሎች ጓደኞችና ዘመዶች እንዲደረስና እንዲያካልላቸው አምነታችን ጽኑ ነው፡፡" መዝግቧል፡፡ ዛሬም የርሳቸው አመራር ለተባበሩት ዓረብ ኢምሬት ጽኑ ራእይና ለሰው ልጆች የማያቋርጥ ስጦታ አስትራቴጂና አይታ ሆና ያገለግላል፡፡

## የሸይኽ ዛይድ ልግስናዎች፡-

ሸይኽ ዛይድ የአቡ ዳቢ ክልላዊ መንግስትን ማስተዳደር ከጀመሩበት ጊዜ አንስቶ አስከ ዛሬ ድረስ አንዴም ልግስናቸው አላቆመም። ሰብኣዊ ድርጊቶቻቸው ከርሳቸው በኋላ ላሉትም አስደናቂ ተምሳሌት ሆኖ ቀርቷል። ሸይኽ ዛይድ በተለያዩ ክስተቶችና ገጠመኞች ውስጥ የቅርቡም የሩቁም የርሳቸው የድረሱልኝ ጥሪ ምላሽ ሰጪ የሆኑ የቁርጥ ቀን ሰው መሆናቸውን አረጋግጠዋል። ሸይኽ ዛይድ የተባበሩት አረብ ኢምሬት ዜጎችንና መንግስታዊ ድርጅቶችን ለሰብኣዊ ድርጊቶች ፈጣን ምላሽን ያቀርቡ ዘንድ አጽድቀዋል። የሸይኽ ዛይድ አባባሎችና ሰብኣዊ ድርጊቶችም በሁሉም ልቦና ውስጥ ሰርጿል። ከዚህ ጋር በተያያዘ መልኩም ሸይኽ ዛይድ ለህዝባቸው ይህን መልእክት ያስተላልፋሉ፦ “ወደፊት የሰውን ልጅ መገንባት ፋብሪካዎችን ከመገንባት በፊት የሚቀደም አሳሳቢ አገራዊና ወገናዊ ጉዳይ ነው። ይህ የሆነበት ምክክንያት ይህ ሁሉ ውጤት ያለ ሰው ምንም ትርጉም ስለሌው ነው።” ሸይኽ ዛይድ በአርግጥም በሰብኣዊ ልግስና እና በበጎ አድራጎት የማያልቅና የማይነጥፍ ምንጭ ነበሩ።

## ኢማራት በሸይኽ አርምጃዎች፡-

የተባበሩት ዓረብ ኢምሬት በአሁኑ ጊዜ የሸይኽ ዛይድን ዱካ በሚከተሉት በሸይኽ ኸሊይፋህ ቢን ዛይድ አመራር ስር አየተራመደች ትገኛለች። የሰብኣዊ በጎ አድራጎቶች ሥራዎችን ለማልማትና ለማሳደግ የሸይኽ ዛይድን ፋና በመከተል ቀዳማዊነትን ለመጎናጸ በጽናት ትሰራለች። አርሳቸው ያስቀመጧቸው መመሪያዎች በህዝቦቻቸው ደም ጅማት ውስጥ ይዘዋወራል። ለዜጎችና ለውጭ አገር ዜጎችም በትሩፋቶቹ ያካልላቸዋል። የኢማራትን ልግስና ልዩ ከሚያደርጉት ነገሮች ውስጥ የተጠቃሚዎቹን ማህበረሰባት የሐይማኖት የዘርና የቀለም ልዩነቶች ላይ አለማተኮሩ ነው። በዋናነት የሚያተኩረው የተቸገሩ ሰዎችን ፍላጎትና ሰብኣዊ ሁኔታዎቻቸውን ግምት በማስገባት ሰብኣዊ ዝንባሌዎቻቸው ላይ በማተኮር ብቻ ነው። ዛሬም አነዚህን የበጎ አድራጎት ሥራዎችን ከተለያዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች የሚቀርቡት ዘገባዎች ያረጋግጣሉ። የልማትና የአርዳታ ድርጅት ተከታይ የሆነው “የ2017 ዓ.ል የልማትና አርዳታ ኮሚቴ” (OECD) ዘገባ አንዱ ነው። የተባበሩት ዓረብ ኢምሬት በዓለም አቀፍ ደረጃ አርዳታ ከሚያቀርቡ አገራቶች የመጀመሪያውን ቦታ ተጎናጽፋለች። ይህም የዓለም አቀፍ የመመዘኛውን መሠረት በሚስማማ መልኩ ነው።

## የኢማራት ሰብኣዊ አርዳታዎች፡-

የተባበሩት ዓረብ ኢምሬት ሰብኣዊ አርዳታዎችን የማቅረብን አስፈላጊነት መሠረት በማድረግ “ኢማራት የውጭ ጉዳይ ሰብኣዊ አርዳታ የማቅረብ ማስተናበሪያ ኮሚቴ” የሚባል ኮሚቴን አዋቅራለች። ይህም የሚኒስትሮች ፓርላማ በ 2014 ዓ.ል ህግ መሠረት የጸደቀ ነው። በዚህ ኮሚቴ አማካይነትም ኢማራት በመንግስትና በህዝብ ደረጃም በዓለም ላይ ሰብኣዊ ጉዳዮችን በመከታተል ግብረገቡ የተሟላ አገልግሎት በማቅረብ ግዴታዋን ለመወጣት አረጋግጣለች።

## ሰብኣዊ አድራጎቶች በኢማራት ውስጥ፡-

የተባበሩት ዓረብ ኢማራት በዓለም አቀፍ ደረጃና በአገር ውስጥ የሥራ ፈቃድ የጸደቀላቸው ምንም አይነት መለያዎችን ሳያደርጉ አርዳታ የሚያቀርቡ የሆኑ ሰብኣዊ አካላቶችና ድርጅቶችን በውስጧ አቅፋለች። ከዚህ በመቀጠልም በኢማራት ውስጥ የሰብኣዊ አድራጎት የሚያቀርቡ ዋና ዋና ድርጅቶችን ስም በዝርዝር አናቀርባለን፦

1. ዛይድ ቢን ሱልጧን ኣል ናህያን የሰብኣዊና የበጎ አድራጎት ድርጅት.
2. ኸሊይፋህ ቢን ዛይድ ኣል ናህያን የሰብኣዊና የበጎ አድራጎት ድርጅት.
3. ኣል መኽቱውም የበጎ አድራጎት ባለስልጣን.
4. ዱባይ ለጋስ ድርጅት.
5. ኢማራት የቀይ ጨረቃ ድርጅት.



እነዚህ ድርጅቶች በተለያዩ ቦታዎች በመዘዋወር የተለያዩ ሰብኣዊ አድራጎቶችን የማቅረብን ግዴታ በመወጣት ይሰራሉ። የሚያቀርቡት አገልግሎትም እንደ ተጠቃሚዎቹ ቀዳሚዊ ፍላጎቶች ይመደባል። ከዚህ ቀደም ከተፈጸሙት የሰብኣዊ አርዳታ ገጽታዎችም፦ የልማት ፕሮጀክቶች፣ የሰብኣዊ አርዳታዎች፣ የድጎማ በጎ አድራጎቶችና ሌሎች በዚህ ዘርፍ የተካተቱትን ያጠቃለለ ነው።

“ዛይድ የሰብኣዊ አድራጎቶች ቀን” የበጎነትና የልግስና እንዲሁም ከኢማራት ወደ ሌላው ዓለም የሚሰራጭ ሰብኣዊ ተነሳሽነት ያለው የጥረት ቀን ሆኖ ዝነት ዓለም ይቆያል። በዚህ ቀን ውስጥ የተባበሩት ዓረብ ኢምሬት አገሪቱን ከመሠረቷትና ከገነቧት ታላቅ መሪ በየ ዓመቱ ቃልኪዳኗን ታድሳለች። የርሳቸውን ፈለግ በመከተል እንደምትሰራም ከመላው ዓለም በጽናት ታረጋግጣለች።

دار زايد للثقافة الإسلامية
Zayed House For Islamic Culture

zhic.uae @zhic_uae zhic_uae zhic

800 555 اتصل على JUST CALL

P.O Box: 16090, Al Ain, U.A.E
www.zhic.ae contact@abudhabi.ae